Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

# የትምህርት ቤት ደህንነት እና የአደጋ ጊዜ ሂደቶች

## ለወላጆች እና ለቤተሰቦች አስፈላጊ መረጃ

### ምን እንደሚጠበቅ እና እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ እወቁ

### ማድረግ ያለብዎት

- **ማድረግ አለብዎት፦-** በአስቸኳይ አደጋ ጊዜ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎችን ማግኘት እንዲችሉ ዘወትር የሚገኙበትን መረጃ ParentSquare ላይ ወቅታዊ ያድርጉት።
- **ማድረግ ያለብዎት፦-** በአስቸኳይ አደጋ ጊዜ ParentSquare እና MCPS ኦፊሴላዊ ግንኙነቶችን ይከታተሉ።
- **ማድረግ ያለብዎት፦-** ከትምህርት ቤቶች ዲስትሪክት እና በአስቸኳይ አደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪዎች የሚሰጡትን መመሪያዎች በሙሉ ይከተሉ።
- **ማድረግ ያለብዎት፦-** ከልጅዎ ጋር የአስቸኳይ አደጋ ጊዜ ሂደቶችን አንብቡ እና ልምምዶችን በቁም ነገር እንዲያከናውን/እንድታከናውን ያበረታቱ።
- **ማድረግ ያለብዎት፦-** የደህንነት ስጋቶችን ለትምህርት ቤት አስተዳደር ወይም ለሜሪላንድ ሴፍ ስኩልስ ቲፕ መስመር/Maryland Safe Schools Tip Line ወዲያውኑ ሪፖርት ያድርጉ።
- **ማድረግ ያለብዎት፦-** አስቸኳይ ስጋት ወይም ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም ወደ 911 ይደውሉ።

### አስፈላጊ ማሳሰቢያዎች

- የአስቸኳይ አደጋ ጊዜ ሂደቶች እንደ ሁኔታው ሊለወጡ ይችላሉ።
- ቤተሰብዎ ትምህርት ቤቶች በአደጋ ጊዜ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን እርምጃዎች ማወቅ እንዲችሉ ስለ መደበኛ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮቶኮል ፈጣን መመሪያ ከልጅዎ ጋር አንብባችሁ ተነጋገሩ።
- ልጆችን ከቤተሰብ ጋር ማገናኘት አስፈላጊ ከሆነ፣ ለተሰቦች ከልጆቻቸው ጋር የሚገናኙበት ቦታ እና መመሪያው በኦፊሴላዊ MCPS የግንኙነቶች መስመር ይደርሳቸዋል።

ስካን አድርገው መደበኛ የአስቸኳይ አደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮቶኮል ይመልከቱ ፈጣን መመሪያ/Quick Gudie

### ማድረግ

- **ማድረግ የለብዎትም፦-** እንዲያደርጉ ካልተነገረዎት በስተቀር**ወደ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ድንገተኛ አደጋ ቦታ መጣደፍ ወይም መሮጥ የለብዎትም** ።
- **ማድረግ የለብዎትም፦-** **ድንገተኛ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ ጥድፊያ ላይ እያሉ ወደ ትምህርት ቤት ቢሮ አይደውሉ።** ሰራተኞች የተማሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ በአደጋ ጊዜ ምላሽ በመስጠት ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው።
- **ማድረግ የሌለብዎት፦-** **የሃሜት ወሬዎችን፣ ፎቶዎችን ወይም ያልተረጋገጡ መረጃዎችን ለሌሎች አታጋሩ።** ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) እና ከአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪዎች በሚሰጡ ኦፊሴላዊ መረጃዎች ላይ ብቻ ይተማመኑ።
- **ማድረግ የሌለብዎት፦-** **ዲስትሪክቱ ቦታውን እና መመሪያዎችን እስኪሰጥ ድረስ** መልሳችሁ ወደምትገናኙበት ቦታ ሂዱ።
- **ማድረግ የሌለብዎት፦-** **ለልጅዎ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም የአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪዎች ከሚሰጡት** መመሪያዎች ጋር የሚጋጩ መመሪያዎችን አትስጡ።

## ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች

**MCPS መደበኛ የአደጋ ጊዜ የመከላከል እርምጃዎች**

- **ባሉበት መቆየት/Hold፦-** ክፍል ውስጥ ወይም በአካባቢ ቆዩ፤ መተላለፊያ ኮሪደሮችን አትዝጉ/ግልጽ አድርጉ።
- **በሮችን መዝጋት/Secure፦-** ሁሉንም ሰው ወደ ውስጥ ማስገባትና የውጪውን በሮች መቆለፍ።
- **በሮችን መቆለፍ/Lockdown፦-** በሮችን መቆለፍ፣ መብራቶቹን ማጥፋት፣ ከእይታ ውጪ መሆን።
- **ለቆ መውጣት/Evacuate፦-** ከትምህርት ቤቱ ውጭ ወደተመደበ ቦታ መሄድ።
- **ከለላ መያዝ/Shelter፦-** የተለየ አደጋ የሚያስከትል ነገር ሲያጋጥም የመከላከል መመሪያዎችን መከተል።

ተማሪዎችና ሰራተኞች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ያድንገተኛ አደጋ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ እንዲሆኑ ትምህርት ቤቶች ዓመቱን ሙሉ ስለ አስቸኳይ የድንገተኛ አደጋ ምላሽ የመስጠት ሂደት ልምምዶችን ያደርጋሉ።

**ስለ ግንኙነት መረጃ ወይም ጥያቄዎች።**

- በሮችን ዘግቶ መቆየትና መቆለፍ ሂደቶች ጥያቄዎች ካሉዎት የትምህርት ቤቱን አስተዳዳሪ ያነጋግሩ።
- የትምህርት ቤትዎን የአደጋ ጊዜ ምላሽ የመስጠት ሂደቶች ይመልከቱ ወይም ስለ ድንገተኛ አደጋ መደበኛ ምላሽ ፕሮቶኮል አውደመረብ/ድረገጽ ይጎብኙ።
- የደህንነት ስጋቶችን በሚመለከት ለትምህርት ቤት አስተዳደር ወይም ስም-ሳይጠቀስ ለሜሪላንድ ሴፍ ስኩልስ ቲፕ መስመር/Maryland Safe Schools Tip Line **1-833-MD-B-SAFE ሪፖርት ያድርጉ።**
- ለአስቸኳይ ድንገተኛ አደጋ ስጋት ወይም ድንገተኛ አደጋ፣ ወደ911 ይደውሉ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምሕርት ቤቶች 2026